# ኢትዮጵያን ያለፌደራሊዝም ማሰብ ይቻል ይሆን?

**(ክፍል አንድ)**

ዮናስ 07/11/14

የዚህ ፅሁፍ መነሻ ሰሞንኛ የሆነው የፓርቲዎች ውህደት ግርግርና አስቀድሞ የከሸፈ ፕሮፖጋንዳ ነው፡፡ ይኸውም ቀደም ብለው መድረክን በመፍጠር ወደ ውህደት በማምራት ዋዜማ ላይ ነን ሲሉ የነበሩ ፓርቲዎች እንደገና እየተፈረካከሱና ከመድረኩ ውጪ ከሆኑት ጋር የቅድመ ውህደት ስምምነት ሲፈርሙ አንዳንዶቹ ደግሞ የብቻዬ ፖለቲካን መዝፈናቸው ነው፡፡ የተቀሩት ደግሞ የቅድመ ውህደት ስምምነት ያደረጉ ፓርቲዎችን "ብዝሃነትን መሰረት ያላደረጉና የአንድ ብሄር ውክልናን በኢትዮጵያዊነት ስም የሚያቀነቅኑ" ሲሉ እየከሰሱና የትም የማያደርስ ጋብቻ ነው ሲሉ ነቀፌታቸውን እያሰሙ ነው፡፡ ውህደቱን እንከን የለሽ ሲሉ የሚያሞካሹ የመኖራቸውን ያህል በዚያው ልክ በፍራቻ ተሳስቦ ተከታዩን ምርጫ ለመሻማት የተደረገ ውህደት ስለመሆኑና ቅድመ ውህደቱም በጠቅላላ ጉባዔ ስለመፅደቁ ጥርጣሬያቸውን በምክንያት በማብራራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም በተለይ በመኢአድ እና በአንድነት ፓርቲ መካካል የተደረገውን ቅድመ ውህደት ስምምነት በተመለከተ የአንድነት ፓርቲ መስራችና ጉምቱ የነበሩ አመራሮች፣ አንድነትን በመድረኩ የሚያውቁትና በተደጋጋሚ እራሱን ያጠራ ዘንድ ሲሞግቱ የነበሩ አመራሮች፣ እንዲሁም ሌሎች ፖለቲካውን በንቃት የሚከታተሉ እና እየታዘቡ የሚገኙ ምሁራኖች ከሰጧቸው አስተያየቶች ውስጥ በሰንደቅ 9ኛ ዓመት ቁጥር 460 ረቡዕ ሠኔ 25/2006 የተመለከተውን እና በፋክት ቁጥር 53 ሰኔ 2006 ላይ የአንድነት መስራች በነበሩትና የመድረኩም ሊቀመንበር ሆነው ያሳለፉትና ፌደራላዊ ስርዓቱን ካዋቀሩት አንዱና በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ለረጅም አመታት በአመራርነት የቆዩት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ‹‹ውህደት፣ ምርጫና አመፅ›› ሲሉ ካሰፈሩት ፅሁፍ አንፃር ተነስቼ የውህደቱን ግርግር ከፌደራላዊ ሥርዓቱ እና በተለይም ከብዝሃነት አያያዝ አኳያ ይህ ፅሁፍ ለማሄስ ይሞክራል፡፡

ውህደቱና ውህደቱን ተከትሎ እየተራገበ ያለው የፕሮፖጋንዳ ቱማታ መነሻው ምርጫ 2007 ነው፡፡ ይህን የምልበት ምክንያት ከላይ የተመለከቱትና ለዚህ ፅሁፍ ግብአት

የሚሆኑኝ ፀሃፊዎችና አስተያየት ሰጪዎች ጉዳዩን ከምርጫ 2007 እና ‹‹ዓመፃ›› አኳያ ማየታቸውን በእርግጥም የውህደቱ ውጥን ምርጫ 2007 መሆኑን ስላመላከተኝ ነው፡፡

ለአብነት ይሆነናል ወይም የዚህ ፅሁፍ መነሻ ነው ያልኩትና ከላይ ቁጥርና ቀኑ የተነመለከተው ሰንደቅ ለጉዳዩ የሰጠው ርዕስም “የ2007ቱ ምርጫና ነጥሮ ያልወጣው የፓርቲዎች አሰላለፍ›› የሚል ሲሆን በዋናነት ደግሞ አንጋፋ ከሆኑት የተቃዋሚ ፓርቲ መስራችና አመራሮች የአቶ ቡልቻ ደመቅሳን ‹‹የሚቆጨን ነገር አንድነት ከእኛ ጋር ሳይጣላ ወደሌላ መሄዱ ነው›› የሚለውን፣ ‹‹የቅንጅትን መንፈስ እንመልሳለን›› የሚለው የአቶ አስራት አብርሃም አስተያየት (የተዋሃጆቹ) “አደጋ አለው” የሚለውንና ‹‹አሁን ያለው የተቃዋሚ ፓርቲዎች አሰላለፍ የተዝረከረከ ነው›› በማለት የአንድነት መስራች የሆኑትን እና በከፍተኛ አመራርነትም ያገለገሉትን የአቶ ሃይሉ አርአያ አስተያየት ማጉላቱ ውህደቱ ከምርጫው አኳያ ትርጉም  የተሰጠው መሆኑን የሚያመላክት ስለሆነ ነው፡፡

ከውህደቱ ጋር ተያይዞ ስማቸው የሚነሳው በዋናነት በመድረኩ ውስጥ ያሉትና ከዚያ ውጪ ደግሞ መኢአድና ሰማያዊ ፓርቲ ናቸው፡፡ በዚህ አግባብ ሰንደቅ ሰሞነኛውን የውህደት ግርግርና አሰላለፍ መጀመሪያ የተመለከተው ከአረና ፓርቲ አንፃር ነው፡፡

የውህደቱን ግርግሮችና መጠላለፎችን ስንመዝን ዋና መለኪያችን ከመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታና ፓርቲዎቹ ማእከል ካደረጉትና ከሚምሉለት ህዝብ አንፃር መሆኑ መዘርጋት የለበትም፡፡ ከዚህ አንፃር ምዘናችንን ወደ አረና ፓርቲ ስናሻግር አረና በተደጋጋሚ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ያደረገበትና በመግለጫ ጋጋታ ዛሬ ነገ ሲለን የነበረው ከደቡብ ህብረት ጋር የጀመረው የውህደቱ ጉዞ በአባላቱ ጉምጉምታ መንገድ ላይ መቆሙን ከአንድነት ጋር ያሰበውም ውህደት “አንድነት ይውጠናል›› በሚል የፓርቲው አመራሮች ስጋት፣ በሌላ በኩልም በአብዛኛው የትግራይ ተወላጅ ዘንድ አረና የትግራይ ፓርቲ ሆኖ በግንባር ከመድረክ ጋር እንዲቀጥል እንጂ ከማናቸውም ጋር ውህደት እንዳይፈፀም ግፊት የተደረገበት በመሆኑ ወዲህና ወዲያ የፖለቲካ ዥዋዥዌ እየተጫወተ እንደሚገኝ ብዙዎች እየተናገሩ ብቻ ሳይሆን ከፓርቲው ጽ/ቤት የሚወጡ መረጃዎችም እያመላከቱ ነው፡፡

በዚህ አግባብ  የአረና ከዚህኛውና ከዚያኛው ጋር እንዳይዋሃድና በሌላ በኩልም በይውጡናል ስጋትና ጉምጉምታ የከሸፈው ውህደት መነሻው ሌላ ሳይሆን ከብዝሃነትና ከፌደራሊዝም አንፃር ለውህደት የታጩቱ እና እራሱንም ያጨው አረና ያላቸው ምልከታና

ልዩነት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ጉምጉምታ፣ መዋዋ ወዘተ የሚሉት ነገሮች የክስረት መጋረጃዎቸ ናቸው፡፡ ስመሆናቸውም የልዩነቱ ምንጭ ብዝሃነትና የፌደራሊዝም እሳቤ መሆኑን ወደኋላ በደንብ በመዘርዘር ማጠየቃችንን ያጤኗል፡፡ አሁን ደግሞ መቼም ሁሉም ፓርቲዎች የሚምሉትና ግዝት የሚገቡት በህዝብና በዴሞክራሲ ስም ነውና ከዴሞክራሲና ከህዝብ ጥቅም አንፃር የፓርቲዎች ውህደት አስፈላጊ ቢሆንም መሰረቱ ህዝብና ዴሞክራሲ ነው የሚለው ሰማያዊ ፓርቲ ደግሞ ከፓርቲዎች ውህደት አንፃር ያለበትን አሰላለፍ እንመልከት፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ ውህደት የሚባል ነገር እንደማይሻና አለመሻቱንም በተደጋጋሚ ከመግለፅ ባለፈ በመርህ ደረጃ ውህደትን ቢደግፍም ‹‹ከማን ጋር›› ሲል ሌሎቹን ፓርቲዎች እንደፓርቲ ትርጉም እንደማይሰጣቸውና በስም እንጂ በአካል የሌሉ እንደሆነም በተደጋጋሚ አሳውቋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአካል የሉም የተባሉት ፓርቲዎች ሰማያዊን “የመረበሽ አንጂ” ሌላ ሚና የሌለው መሆኑን ሲያወሱ በተለይ አቶ ቡልቻ ደመቅሳን የመሰሉ አንጋፋ ፖለቲከኛ ሰማያዊ ፓርቲ እንደፓርቲ ‹‹ሊገባቸው እንዳልቻለና ሊረዱትም እንዳልቻሉ›› ለሰንደቅ ጋዜጣ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ አቶ ቡልቻ አለመረዳታቸውን የበለጠ ሲያብራሩም ‹‹የእነሱን ዓላማ ገብቶኝ አላኘኩትም፡፡ ለማወቅ ግን ሞክሬያለው፡፡ ለእኔ ጨለማ ነው፡፡ በእግርጥ ኢትዮጵያን ያለፌደራሊዝም ማሰብ አይቻልም፡፡ አስር ጊዜ ቢጮኽ አይሆንም፡፡ ይሄ መታወቅ አለበት›› በማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ እንግዲህ ከውህደት ጋር ተያይዞ የሰማያዊ እምቢኝ ማለትና ሌሎቹን ማራከስ ለፌደራሊዝም ካለው እይታና አሃዳዊ ስርዓትን የሚሻ ከመሆኑ የሚመነጭ እንደሆነ የሚያመለክት አስተያየት ሲሆን፤ ይልቁንም ኢትዮጵያን ያለፌደራሊዝም በጩኸት መገንባት ቀርቶ ማሰብም የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ በሌላ በኩልም ሰማያዊ ፓርቲ የባልና የሚስት አይነት ጠብ ከአንድነት ጋር መፍጠሩን የሚናገሩ ወገኖች የጠቡን ምክንያት በቂ የሆነ የፖለቲካ ብስለት፣ የፓርቲ አደረጃጀትና አሰራር እንዲሁም ብቃት ያለው ሰው በፓርቲው ውስጥ አለመኖሩ ነው ቢሉም፤ ይህን የሚሉትም በዚሁ ዓውድ ስር የሚገኙ መሆናቸውን እና ይልቁንም ከመኢአድ  በላቀ ደረጃ ፌደራሊዝምን ውጪ ለማቆየት የሚሹ ስለመሆናቸው ከአንድነትና የመኢአድ ቅድመ ውህደት አንፃርና የውህደቱ መነሻ ምክንያቶች አንፃር ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

የሁለቱም ፓርቲዎች ቅድመ ውህደት ከመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት አኳያ ከሚኖረው ተስፋ ይልቅ ስጋቱ እንደሚያመዝን የሚገልፁት ወገኖች መኢአድ በምርጫ 97 ወቅት በቅንጅት ዘንድ የነበረውን የጎላ ተፅዕኖ ምክንያት በማድረግ ምርጫ 2007ን በቅንጅት መንፈስ ህዝብን ተገገር ለማድረግ ያለመ በመሆኑ በምክንያትነት በማቅረብ ነው፡፡

ቀድሞ ነገር አንድነት የመድረኩ ጠንሳሽ፤ የመድረኩ አባል ፓርቲዎችን ወደ ውህደት ለማምጣት ሲዳክር የነበረ ቢሆንም ለብዝሃነት አያያዝ ካለው ምልከታና ከፌደራሊዝም ጋር ካለው የማይቀለበስ አቋም በተነሳ (በግልፅ ባይናገረውም) ከመድረኩ አባል ፓርቲዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ትቶ ከመኢአድ ጋር መዋሃዱ፣ መኢአድም በበኩሉ በመድረኩ ውስጥ ያሉ የሚበዙ ፓርቲዎች በፌደራሊዝም እና ብዝሃነት ጉዳይ ከገገር ፓርቲ ጋር ተመሳሳይ አቋም ያላቸው መሆኑን (ከላይ የተመለከተውን የአቶ ቡልቻ ደመቅሳ አስተያየት ያስታውሷል) በግልፅ በመናገርና ‹‹አንድነት ከመኢአድ ጋር እንዲዋሃድ የሚሻ ከሆነ ከመድረኩ መጀመሪያ መውጣት አለበት›› የሚለው የመኢአድ አቋም ስለፌደራሊዝም ያለውን ምልከታ የሚያስገነዝብ ሲሆን ይልቁንም አንድነት የአማራ ብሄርተኝነትን ማቀንቀኑን እና በይፋ አለመናገሩን ጠቅሰው ለመድረኩ ወደ ውህደቱ አለመምጣት እንቅፋትነቱን ሲገልፁና ሲከሱ የነበሩ የመድረኩ አባል ፓርቲ አመራሮች አስተያየት ትክክል መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ይህን በተመለከተ እና የሁለቱ ፓርቲዎች ቅድመ ውህደት ከምርጫ 2007 አንፃር ያላቸውን ፖለቲካዊ ግምገማ በሰንደቅ የተጠየቁቱ አቶ አስራት አብርሃም ሲመልሱ አንድነት የመሀል ፖለቲካ ባህሪ ያዘለ መሆኑ፣ ለብሄሮችና ብሄረሰቦች እውቅና አለመንፈጉ፣ የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ውክልና ለመያዝ የሄደበትን እርቀት አንደያዘ የሚቀጥል ከሆነ ጥሩ ውህደት ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ይህ እንግዲህ ለብሄሮችና ብሄረሰቦች እውቅና መስጠት ምን ማለት ነው? የሚለው ጥያቄን ያልመሰለሰ መሆኑ አሁንም የአንድነትን ችግር የሚያሳይ ነው፤ እውቅናና ዋስትና ይለያያሉና፡፡ ሌላው የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ውክልና እንደያዘ የሚቀጥል ከሆነ ማለታቸውንም ስናጠይቅ የኢትዮጵያዊነት ውክልናን ትርጓሜ ትተን ቢያንስ አንድነት ለብሄሮችና ብሄረሰቦች ወይም ፌደራሊዝም ይቀበላል እንኳ ቢባል መኢአድ በበኩሉ ለብሄር ብሄረሰቦች ዋስትናውም ቀርቶ እውቅናም እንደማይሰጥ መገለጡ ስለአንድ ብሔር

አቅንቃኝነቱ የተሰጠ ማረጋገጫ ነው፡፡ ስለሆነም አንድነት ከዚህ ፓርቲ ጋር ተዋሃደ ማለት ይህንኑ ማረጋገጡንና ኢትዮጵያን ያለፌራሊዝም ማሰቡን የሚያመላክት ሲሆን ይህ ከሆነ ደግሞ አቶ ቡልቻ እንዳሉት በተደጋጋሚ ቢጮህም የማይሳካና የትም የማያደርስ ነው፡፡ ለምን? ቢሉ ኢትዮጵያን ከብዝሃነት አያያዝና ከፌደራሊዝም ስርአት አንፃር ውህደቱን የተመለከቱ አስተያየቶችን ከጨረስን በኋላ የምናው መሆኑን ለማስታወስ እሻለሁ፡፡

አቶ አስራት ሲቀጥሉም ‹‹የቅንጅትን መንፈስ እንመልሳለን›› የሚለውን የተዋሃጆቹ ፕሮፖጋንዳ አደጋ እንዳለው ሲነግሩን ‹‹አዲሱ ውህድ ፓርቲ በትዝታ የሚቆዝም ሳይሆን በተስፋ የተሞላ ፕሮግራምና መሪ ያስፈልገዋል . . . አዲሱን ፓርቲ የሚመራ ባለራዕይ መሪ ያስፈልጋል . . . በትዝታ ሳይሆን በተስፋ የተሞላ፣ ሰፋ አድርጎ የሚያስብ፣ የኢትዮጵያውያንን ስሜት በሚያንፀባርቅ መልኩ የተቃኘ አመራር ያለው ፓርቲ መሆን አለበት፡፡ [. . . ] ጥሩ አደረጃጀትና ተቋማዊ ቅርፅ ቢኖርም ያለ ጥሩ ፕሮግራምና ቆራጥ መሪ ውጤታማ ሊሆን አይችልም››

ይህ ማለት የአንድነቱ አቶ አስራትም አንደነ አቶ ቡልቻ ያለፌደራዝምና ብዝሃነት ኢትዮጵያዊነትን እና ኢትዮጵያን ማሰብ ከንቱ ድካም መሆኑን የሚገልፅ አንደምታ ያለው አስተያየት ሲሆን ውህደቱም ምርጫ 2007ን ብቻ ታሳቢ አድርጎ በቅንጅት መንፈስ ለመመራት የሚሞክር፤ ተቋማዊ ቅርፅ ቢኖረውም ባለራዕይ መሪና ፕሮግራም የሌለው መሆኑን በግልፅ የሚያረጋግጥ ምስክርነት ነው፡፡ ይህ በግልፅ የተመለከተውና ፕሮግራም አልባና ቆራጥ መሪ ያጣ እንዲሁም በተስፋ የተሞላ ሳይሆን በትዝታ የሚቆዝም ፓርቲ ከላይ በተመለከተውና ሰማያዊ ፓርቲን ባጠየቅንበት ቦታ ላይ ሰማያዊን “ብስለትና ዕውቀት በሌለው ስብስብ የተሞላ” ለሚለው ወቀሳ የአፀፋ ምላሽ እንጂ ምንም እንዳልሆነ የሚያመላክትና ሰማያዊ በአንድነት የተገለፀውን እንኳን ቢሆን አንድነትም በዚህና በአቶ አስራት አብርሃም የምስክርነት ቃል በተመሳሳይ ደረጃ ላይ መሆኑ ለክስና ለፍረጃ የሚያበቃ የፖለቲካም ሆነ የሞራል ብቃት የሌለው መሆኑን የሚያረጋግጥልን እውነታ ነው፡፡

አቶ ቡልቻም በተመሳሳይ መልኩ የአንድነትን ከመኢአድ ጋር መዋሃድ በተመለከተ መሳሳቱን እና የደቡብ ህዝቦችንና ኦሮሚያን ተነጥሎ የትም እንደማይደርስ ማውሳታቸው ከምርጫ አኳያ ከሚገኝ ድምፅ ብቻ ሳይሆን መተርጎም ያለበት አንድነት በግልፅ የማይናገረውን አቶ አስራት በዘወርዋራ የተናገሩትና የአንድነት ኢትዮጵያዊነት ፌደራላዊ

ስርዓትና ብዝሃነት ሳይሆን አንዲት ኢትዮጵያ አንድ ባንዲራና አንድ ቋንቋ እንደሆንም ጭምር ነው፡፡ ዶ/ር ሃይሉ አርአያም ለሰንደቅ በሰጡት ቃል ውህደቱ ባይጠላም ግቡ ካደረገው ምርጫ 2007 አኳያ "የተዝረከረከ" አሰላለፍ መሆኑን በመጥቀስ *የተበላ እቁብ ነው* ማለታቸው የፓርቲዎቹ ችግር ምርጫ 2007ን ያለብዝሃነትና ፌደራሊዝም ማሰባቸውና የሚምሉለትን ህዝብ አለመምሰላቸው እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

የአንድነትና የመኢአድን ቅድመ ውህደት ‹‹ውህደት ምርጫና አመፅ›› በሚለው መጣጥፋቸው ላይ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በራሱ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ልማድ ውስጥ ካለው የድርቅና አካሄድ አንፃር  በነ ጅምር እንዲሆነ ይገልፁና ከአደረጃጀት ጋር የተያያዙትን እና ካለ ፌደራሊዝምና ብዝሃነት ኢትዮጵያን በውህደት መገንባት የማይቻልበትን እንዲሁም ውህደቱም ከድርቅና ፖለቲካ አንፃር ካለው ትርፍ የዘለለ ፋይዳ የሌለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሚስጥር እንዲህ ይገልፃሉ፡፡

‹‹ለምሳሌ አንድነትና መኢአድ የተሰኙ ፓርቲዎች ሁለቱም የፌደራል ስርዓቱን የሚቃወሙና የሊበራል ፖለቲካ ሀሳብ ደጋፊ በመሆናቸው የተቀባይነት እድላቸውን ይገድበዋል፡፡ በግልፅ እንደሚታየውም የፓርቲዎቹ ተቀባይነት በአማራው አካባቢ የተገደበ ነው›› እንግዲህ ዶ/ር ነጋሶ ስለፌደራላዊ ስርዓት በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አሰላለፍ ውስጥ በርካታ ዘመን በማሳለፋቸው ጠንቀቀው የሚያውቁትና የተቀባይነቱን ደረጃና ህዝባዊ መሰረቱን ለመረዳት የማይከብዳቸው መሆኑ ግልፅ መሆኑን እየሳታወስን፤ በአናቱም የአንድነት መስራች እንደመሆናቸው የአንድነትን አሰላለፍ አቶ አስራት ‹‹እውቅና›› ሲሉ የጲላጦስ እጃቸውን ቢታጠቡም እና አቶ ቡልቻ *ደቡብና ኦሮምያን ትቶ* ሲሉ በዘወርዋራ ቢነግሩንም ዶ./ር ነጋሶ ግን የአንድነትም ሆነ የመድረኩ ሊቀመንበርና መስራች ከመሆናቸው አንፃር ሚስጥሩና ትክክለኛው አስተያየት የእርሳቸው መሆኑን ማረጋገጥ አይከብድም፡፡ ስለሆነም ዶ/ሩ እንደሚሉትና ካላቸው ልምድ መገመት የሚቻለው ያለፌደራላዊ ስርዓት ኢትዮጵያን በየትኛውም አግባብ ለመገንባት እና ስልጣን ላይ ለመውጣት የማይቻል መሆኑን ነው፡፡

ዶ/ር ነጋሶ ለትርክታቸው ከሰጡት ርዕስ አንፃር ስርዓቱ በምርጫ እንደሚያጭበረብር አምነውና ተቀብለው ስለአመፃ ማውሳታቸው ባይገርምምና ተገቢ ቢሆንም፤ የተቃዋሚዎቹ ዋና ችግር የገዢው ፓርቲ ማጭበርበር ወይም እነርሱ እንደሚሉት በተደጋጋሚ ለመሰነጣጠቃቸው "ኢህአዴግ አባሎቻችንን በገንዘብ እየደለለ ነው" ቢሉም በእርግጥ ገዢው

ፓርቲ እንደተባለውም አድርጎት እንኳ ቢሆን ቁርጠኝነት፣ ፅናትና ታማኝነት እንዲሁም መስዋእትነት የፖለቲካና የፖለቲከኛነት ሀሁ ከመሆኑ አንፀር ክሱ ማረፍ የሚገባው እራሳቸው ላይ መሆኑ ሊሰመርብት ይገባል፡፡ ምን ሲደረግ ቁርጠኛ የሆነ ታማኛና የአላማ ፅናት ያለው ሊያውም በገንዘብ ድለላ ይቅርና ሕይወቱንም መስዋእት ማድረግ ይገባዋል እንጂ፤ ለማስተባበያም የማይመጥን ነው፡፡ ይህንንም ይመስለኛል አቶ ሃይሉ “የተዝረከረከ” የሚሉት፤ አቶ አስራትም ተቋማዊ ቅርፅና አደረጃጀትም ያለ ብቁና ቆራጥ መሪ ዋጋ የሌለው መሆኑንም የጠየቁት ለዚሁ እንደሆነ መገመት አይከብድም ፡፡

ስለሆነም በዚህ አግባብ ውድቅ የሚሆነውን አስተሳሰብና ‹‹የኢህአዴግ የተበላ ሴራ›› በማሳበብ አመጽን እንደ አማራጭ ለመውሰድ የሚቃጡ ፓርቲዎችን ጭምር ዶ/ር ነጋሶ የሚወቅሱት የብዙሃነትን አመክንዮ በማጣቀስ ነው፡፡ በተለይም ይህን ትርክት ያቀረቡበት ፋክትና አምደኞቹ በሰሜን አፍሪካ የታየውን ህዝባዊ ቁጣና አመጽ በኢትዮጵያ ይቀጣጠል ዘንድ መሻታቸውን በማስታወስ፡፡ እንዲህ  ሲሉ፡-

*በሰሜን አፍሪካ የታየው ህዝባዊ ቁጣና አመጽ በኢትዮጵያ ይቀጣጠል ዘንድ ማገዶዎቹ አሉ ብዬ አላምንም፤ የማህበረሰቡን ንቃተ ህሊና በማሳደግና መረጃዎችን በማንሸራሸር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ተብሎ የሚታመነው ፕሬሱ ነው፡፡ ይህም ዘርፉ በራሱ በብዙ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች የተተበተበ ነው፡፡ ኢትዮጵያ እንግዲህ እንደሚታየው በርካታ የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪ ብሄር ብሄረሰቦች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ በግልጽ እንደምንገነዘበውም የተዳፈነውን ህዝባዊ ቁጣ ለማቀጣጠል ደፋ ቀና እያለ የሚገኘው  የግሉ ፕሬስ ነው፡፡ ነገር ግን በርካታ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባሉባት ሃገር በአማርኛ ቋንቋ ብቻ ለዚያውም በውስን ቅጂዎች አማካኝነት እንዴት አድርጎ ነው በጠቅላላው ህዝብ ዘንድ የጋራ አረዳድ መፍጠርና ወደ አደባባይ መጥራት የሚቻለው?*

የተዳፈነ ቁጣ ይኑር አይኑር ባናውቅም ዶ/ር ነጋሶ እንዲሚሉት የአመጽ የማቀጣጠያ ማገዶው መረጃ የሚሰራጭበት አግባብና በዋነኝነት ፕሬሱ መሆኑ ነው፡፡ ፕሬሱ ደግሞ እንደ ፓርቲዎቹ ኢትዮጵያን ካለፌደራላዊ ሥርዓት የተረዳ በመሆኑ ውስንነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ቋንቋ ብቻ የሚታተም መሆኑ የብዙሃነትን አያያዝ አልተረዳምና ከተማ ለከተማ ያለው ጩኸት ከሚበዛውና የብዙ ቋንቋ ባለቤት ከሆነው ህዝብ አንጻር ኢምነት መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ምሳሌው ለአመጽ ቢሆንም በፓርቲዎቹም ሆነ በፕሬሱ ያለው የፌዴራላዊ ሥርዓት እይታ የተዛባ ከመሆኑም በላይ እግረ መንገዱንም ፕሬሱ ከህግ ከታሰበውና ከመርህ አኳያ ከሚኖረው ሥነምግባር ባሻገር የፖለቲካ ሥራ

ውስጥ ስለመግባቱና ተቃዋሚዎቹም የጋዜጠኝነት ተግባር ላይ መዳከራቸውንም የሚያመላከት ነው፡፡

የኢትዮጵያን ሁኔታና የኢትዮጵያዊያንን ማንነት ከመገንዘብና አዋጩም ፌዴራላዊ ሥርዓት መሰረት ያደረገ ተቃውሞ፤ ለብዝሃነትም ዋስትና የሰጠ ተቃውሞ መሆን ሲገባውና ይህ አለመሆኑ በራሱ ኪሳራው የበዛ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ላይ ደግሞ አሜሪካና ምዕራባውያንን እንደመተማመኛ የመውሰዱ እና ከህዝቡ ባልተናነሰ ወሳኝ ክፍሎች እንደሆኑ አድርጎ የመመልከታቸው አዝማሚያ የትም እንደማያደርሳቸውም የታወቀ ነው፡፡ የተለያዩ ሰበቦችን ቢደረድሩም የውድቀታቸው መነሻ ከፌዴራላዊ ሥርዓቱ ውጪ መቆማቸውና ስለብዝሃነት ያላቸው የተዛባ ምልከታ እንደሆነ ከላይ የተመለከቱት እና በፓርቲ አመራሮች የተሰጡት አስተያየቶች ያረጋግጣሉ፡፡ ስለሆነም ውህደቱ በራሱ የአንድ ሰሞን ወሬ እንጂ ያለፌዴራለዊ ሥርዓትና ብዝሃነት የሚቆምበት መሬት እንደሌለው በዚህ አግባብ በመጠኑ ካረጋገጥን ከገዢው ፓርቲና ከኢትዮጵያውያን አንጻር ከምርጫ በመለስ ፌዴራሊዝምና ብዝሃነት ምን ማለት እንደሆኑ በማጠየቅ እግረመንገድም የተቃዋሚዎቹን በተለይም ተዋሃድን ሲሉ ከበሮ መደለቃቸውን ያላቆሙትን ፓርቲዎች *በክፍል 2* የምንፈትሽና በጎውንም የምናመላክት ይሆናል፡፡